# ፍትህ ለጌዲዮ









መጣልን ያልነው ሰው - ተስፋ የጣልንበት
የኦሮሞው ጠቅላይ - ፅንፍ አነገሰበት
ፍትህ ለጌዲዮ - ኢትዮጵያዊ ዜጋ
ተገቢ መሆኑ - በአብይ አይዘንጋ
አፈናቅሎ አስርቦ - የተጨከነበት
የጌዲዮ ድሀ - ምን ጥፋት ታየበት?
አቅመ ቢስ ረግጦ - ግዛት ማስፋፋት
በረሃብ ቸነፈር - ሲያልቁ ሕፃናት
ነግ በኔ ነውና - ይታሰብበት!
በአፉ እየደለለ - አገር አሰግዶ
በሸፍጥ ጨረሰን - በነገድ አሳዶ
የዚህ ሁሉ ህፃን - ጉስቁልና ስቃይ
እርሀብና ጥማት - በጥሞና ይታይ
ምግብና ውሀ - ፍትህ አትንፈጉ
ማዘን መራራት ነው - የሰውነት ወጉ

ዘውዲቱ የማነ

2019-03-11